የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 11
ADDIS ABABA 26th December 2012

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፸፭/፪ሺ፭ ዓ.ም.

የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት
ደንብ............................................................ገጽ ፮ሺ፯፻፬
ሠንጠረዥ..........................................................ገጽ ፮ሺ፯፻፮

CONTENTS

**Regulation No. 275/2012**

Accreditation Service Fee Council of Ministers
Regulation........................................ Page 6704
Schedule........................................... Page 6706

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸፭/፪ሺ፭

## የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ክፍያን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ክፍያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፸፭/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩/ "አክሬዲቴሽን"፣ "የተስማሚነት ምዘና"፣ "የተስማሚነት ምዘና አካል" እና "የክትትል ግምገማ" በኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፭/፪ሺ፫ አንቀጽ ፪ የተሰጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸዋል፤

፪/ "የሰነድ ምርመራ" ማለት ለመስክ ግምገማ የሚሆኑ የተስማሚነት ምዘና አካል ሰነዶችን ተስማሚነት፣ ብቁነትና ውጤታማነትን ማረጋገጥ ነው፤

፫/ "ቅድመ ግምገማ" ማለት የተስማሚነት ምዘና አካል ለአክሬዲቴሽን መስፈርቶች ያለውን ዝግጁነትና መቀራረብ ለማረጋገጥ የሚደረግ ግምገማ ነው፤

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 275/2012

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR FEE OF ACCREDITATION SERVICE

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010.

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Accreditation Service Fee Council of Ministers Regulation No. 275/2012."

**2. Definitions**

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "accreditation", "conformity assessment", "conformity assessment body" and "surveillance audit" shall have the meanings assigned to them under Article 2 of the Ethiopian National Accreditation Office Establishment Council of Ministers Regulation No. 195/2010;

2/ "document review" means verification of the suitability, adequacy and effectiveness of documents of a conformity assessment body for the on site assessment;

3/ "pre-assessment" means assessment carried out to ensure a conformity assessment body's readiness and closeness to the accreditation requirements;

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፬/ "የመነሻ ግምገማ" ማለት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚደረግ ግምገማ ነው፤

፭/ "መስፈርት ምርመራ" ማለት የተስማሚነት ምዘና አካል በተስማሚነት ምዘና ሥራ ለመሠማራት የሚያበቁትን ዝቅተኛ መስፈርቶች ማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚደረግ ምርመራ ነው፤

፮/ "መሪ ገምጋሚ" ማለት የተወሰኑ የግምገማ ክንዋኔዎችን በበላይነት የሚመራ ነው፤

፯/ "የቴክኒክ ገምጋሚ" ማለት በአንድ አክሬዲቴሽን አካል ተመድቦ ብቻውን ወይም የአንድ ቡድን አካል ሆኖ የተስማሚነት ምዘና አካልን የሚገመግም ሰው ነው፤

፰/ "ኤክስፐርት" ማለት በአንድ አክሬዲቴሽን አካል ተመድቦ የሚገመገመውን የአክሬዲቴሽን ወሰን በሚመለከት የተለየ እውቀት ወይም ሙያ የሚያበረክት ሰው ነው፡፡

## ፫. የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ክፍያ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሬዲቴሽን ጽሕፈት ቤት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፭/፪ሺ፫ መሠረት ለሚሰጠው የአክሬዲቴሽን አገልግሎት የሚያስከፍለው ክፍያ ከዚህ ደንብ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ በተመለከተው መሠረት ይሆናል፡፡

## ፬. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ኃይለማርያም ደሳለኝ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

4/ "initial assessment" means assessment to be carried out for the first time;

5/ "checking of requirements" means checking whether the minimum requirements to engage in the business of conformity assessment have been fulfilled by a conformity assessment body;

6/ "lead assessor" means assessor who is given the overall responsibility for specific assessment activities;

7/ "technical assessor" means person assigned by an accreditation body to perform, alone or as part of an assessment team, to assess conformity assessment body;

8/ "expert" means person assigned by an accreditation body to provide specific knowledge or expertise with respect to the scope of accreditation to be assessed.

## 3. Accreditation Service Fees

The fees for the accreditation services provided by the Ethiopian National Accreditation Office pursuant to the Council of Ministers Regulation No. 195/2010 shall be as prescribed in the Schedule attached hereto.

## 4. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, this 26th day of December, 2012.

HAILEMARIAM DESSALEGN

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

## ሠንጠረዥ

## የአክሬዲቴሽን አገልግሎት ክፍያ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት | ክፍያ (ብር) | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| ፩ | የሰነድ ምርመራ | ፫ሺ.፭፻ | |
| ፪ | የቅድመ ግምገማ | ፬ሺ. | የሚላከው አንድ የቴክኒክ ገምጋሚ ለአንድ ቀን፡፡ ምርመራው ከዚህ በላይ የሰው ሀይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ጊዜና የሰው ሀይል ተባዝቶ ይሆናል፡፡ |
| ፫ | የመነሻ ግምገማ | ፯ሺ. | የሚላከው አንድ መሪ ገምጋሚ፣ አንድ የቴክኒክ ገምጋሚና እንደአስፈላጊነቱ አንድ የቴክኒክ ኤክስፐርት ለአንድ ቀን፡፡ ግምገማው ከዚህ በላይ የሰው ሀይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ተጨማሪ ጊዜና የሰው ሀይል መጠን ከፍ ይደረጋል፡፡ |
| ፬ | የመስፈርት ምርመራ | ፪ሺ. | የሚላከው አንድ መሪ ገምጋሚና አንድ የቴክኒክ ገምጋሚ ለአንድ ቀን፡፡ ግምገማው ከዚህ በላይ የሰው ሀይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ተጨማሪ ጊዜና የሰው ሀይል መጠን ከፍ ይደረጋል፡፡ |
| ፭ | የክትትል ግምገማ | ፯ሺ. | የሚላከው አንድ መሪ ገምጋሚ፣ አንድ የቴክኒክ ገምጋሚና እንደአስፈላጊነቱ አንድ የቴክኒክ ኤክስፐርት ለአንድ ቀን፡፡ ግምገማው ከዚህ በላይ የሰው ሀይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ተጨማሪ ጊዜና የሰው ሀይል መጠን ከፍ ይደረጋል፡፡ |
| ፮ | ተጨማሪ ዩኒት ለሚፈ ልጉ ሰፋፊ ላቦራቶሪዎች ግምገማ | ፫ሺ. | የሚላከው አንድ መሪ ገምጋሚ ወይም አንድ የቴክኒክ ገምጋሚ ለአንድ ቀን፡፡ ግምገማው ከዚህ በላይ የሰው ሀይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ጊዜና የሰው ሀይል ተባዝቶ ይሆናል፡፡ |
| ፯ | በግምገማ ወቅት መሰ ረታዊ ጉድለት ያሳየ መልሶ መስተካከሉን ማረጋገጥ | ፫ሺ. | የሚላከው አንድ መሪ ገምጋሚ ወይም አንድ የቴክኒክ ገምጋሚ ለአንድ ቀን፡፡ ግምገማው ከዚህ በላይ የሰው ሀይል ወይም ጊዜ የሚወስድ ከሆነ ክፍያው በሚወስደው ጊዜና የሰው ሀይል ተባዝቶ ይሆናል፡፡ |

## SCHEDULE

## ACCREDITATION FEES

| No. | Service | Fee (Birr) | Remark |
|---|---|---|---|
| 1 | Document Review | 3500 | |
| 2 | Pre-assessment | 4,000 | One technical assessor for one day. If the review requires more man-days, the fee shall be multiplied by the number of man-days. |
| 3 | Initial Assessment | 6,000 | A team comprising one lead, one technical assessor and, as required, one technical expert for one day. If the assessment requires more man-days, the fee shall be increased proportionately. |
| 4 | Checking of Requirements | 2,000 | A team comprising one lead and one technical assessor for one day. If the assessment requires more man-days, the fee shall be increased proportionately. |
| 5 | Surveillance Audit | 6,000 | A team comprising one lead, one technical assessor and, as required, one technical expert for one day. If the assessment requires more man-days, the fee shall be increased proportionately. |
| 6 | Assessment for Additional Units | 3,000 | One lead or one technical assessor for one day. If the assessment requires more man-days, the fee shall be multiplied by the number of man-days. |
| 7 | Clearing Major Non-Conformance | 3,000 | One lead or one technical assessor for one day. If the assessment requires more man-days, the fee shall be multiplied by the number of man-days. |